ዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ.
Zemen Insurance S.Co.

# የጉባኤ ጥሪ

## ለዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366(1) ፣ 367(1)፣ 370 እና 393 እንዲሁም በኩባንያው መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 14 መሠረት የዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ የባለአክሲዮኖች 7ኛ መደበኛ እና 6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ቅዳሜ የካቲት 22 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በግዮን ሆቴል ሳባ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ይካሄዳል፡፡

በመሆኑም የኩባንያው ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔው ላይ እንዲገኙ የኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክብሮት ጥሪውን እያስተላለፈ በንግድ ህግ አንቀጽ 380 መሰረት የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪዎች ተሰይመው እና ምልዓተ-ጉባኤው መሟላቱ ተረጋግጦ ጉባኤዎቹ የሚጀመሩ መሆኑን ይገልፃል፡፡

## 1. ማኀበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1 የኩባንያው አድራሻ ፤ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 2፣ የቤት ቁጥር፡ 3140 ፣ አለም ህንፃ

1.2 የኩባንያው የምዝገባ ቁጥር፤ የንግድ ምዝገባ ቁጥር MT/ AA/3/0051867/2012፤ የመድን ሥራ ፈቃድ ቁጥር 020/20፣

1.3 የኩባንያው የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፤ ብር 500,000,000.00

1.4 የኩባንያው ድረ-ገፅ www.zemeninsurance.com

## የ7ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. አጀንዳ ማፅደቅ፣
2. ከ 6ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በኂላ የተደረጉ የማህበሩን አክሲዮን ዝውውሮች እና አዳዲስ አክሲዮን የገዙ ባለአክሲዮኖችን መቀበል፣
3. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ፡፡

## የ6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. አጀንዳ ማፅደቅ፤
2. የማኀበሩን መመስረቻ ፅሑፍ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 2 ካፒታልና አክሲዮኖችን በተመለከተ ማሻሻያ ማድረግ፤
3. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ፡፡

## ማሳሰቢያ

1. ባለአክሲዮኖች ወይም ተወካዮች ለስብሰባ በሚመጡበት ወቅት ማንነታቸውን የሚገልፅ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ፣ፓስፖርት ወይንም መንጃ ፍቃድ ዋናውን እና ቅጂውን ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. በጉባኤው ላይ በአካል የማይገኙ ባለአክሲዮኖች በንግድ ህግ አንቀፅ 373 መሠረት በወኪሎቻቸው አማካይነት መሳተፍ የሚችሉ ሲሆን፤ ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀናት በፊት የኩባንያው ዋና መ/ቤት ቀርበው ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀውን የውክልና መስጫ ቅፅ በመፈረም ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የውክልና ማስረጃ በያዘ ተወካይ አማካይነት በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፤
3. በባለአክሲዮኖች የተሰጠ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ማስረጃ የያዛችሁ ተወካዮች፤ በጉባኤው ለመካፈልና ድምፅ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ስልጣን ማስረጃ ዋናውና ቅጂውን ይዛችሁ በመቅረብ በጉባኤው ላይ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡
4. በባለአክሲዮኖች የተሰጠ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ውክልና በመያዝ የራስን አክሲዮን ጨምሮ ከማኀበሩ የተፈረመ ካፒታል 10 % በላይ መወከል አይቻልም፤

**የዘመን ኢንሹራንስ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ**